ሐዋርያ፥ ቅጽ 14፥ ቁ 1

መስከረም/ጥቅምት 2001

## ርዕሰ አንቀጽ

# ሞራል ያልገደበው ሥልጣኔ መዘዝ፤

ሰውን ሰው ያሰኘው ወይም ሰውን ከእንስሳት የለየው፥ በዳበረ አእምሮአዊ ስሌቱ ጥሮ ግሮ ማደሩ ነው ቢባልም፥ ሌላው መለኪያው ደግሞ ማህበራዊ ትስስሩ ወይም ሞራላዊ ብቃቱ መሆኑም መዘንጋት የለበትም፡፡ በዓመተ ፍዳ ይባል ወይም በዓመተ ምህረት ይለካ፥ ህብረተሰብ በተጓዘበት ረጅም የታሪክ ሂደቱ፥ አስቦ የማደርና ፈጥሮ የማዳበር ችሎታው መሠረታዊ ኑሮውን ለማሸነፍ ቢያስችለውም፥ ጥቂቶች ከልካቸው እያለፉ አለአግባብ ጥቅምንና የበላይነትን በመሻት በአብዛኛው የጋራ ህይወት ላይ አደጋ ሲያጠሉበት ኖረዋል፡፡ የጥፋት ዘመን ይበሉት አውዳሚ ታላላቅ የዓለም ጦርነቶች፥ የኢኮኖሚ ድቀት ይሁን የከባቢ አየር ብክለት ከሰው ልጅ አልጠግብ ባይነት ፍላጎት፥ ከልክ ያለፈ ስግብግብነትና ዕብክር የነተቡ ናቸው፡፡ የተወሰኑ የማህበረሰቡ አባላት የማይናቅ ተጽእኖ በማሳደር ያለማቋረጥ በሚያሾሩት የህብረተሰብ ታሪክ ሂደት ላይ፥ ማህበራዊ ትስሥሮች እየላሉ፥ ለሌሎች የማዘን፥ የመራራትና የመተሳሰብ ባህርይዎች የሞኝነት መለኪያ እየመሰሉ፥ በአኳያው ግን አንዱ በሌላው ላይ እየተረማመደ የሰው ልጅ የጋራ ተፈጥሯዊ ባህርይ የሆነውን የህሊናን ህገ-ደምብ (ሞራል) በመሻር በማጭበርበርና በመቅጠፍ ከመጠን ያለፈ የግል ጥቅም ማሳደድ፥ ነግቶ እስኪመሽ በሃብት ላይ ሃብት፥ በዝና ላይ ዝና ለማካበት የሚደረገው ጥድፊያ መላውን ህብረተሰብ ወጥመድ ውስጥ በማስገባት ፍዳ ተሸካሚ አድርጎታል፡፡

በአሁኑ ወቅት በዓለም ላይ እውን ሁኖ እየታየ ያለው የሃብት ክምችት ቀውስ፥ መሠረቱ የሞራልና የግላዊ ጥቅም መስተፃምር መዛባቱ ነው፡፡ ሥነልቦናዊና ማህበራዊ ምርኩዝ የጎደለውና በጥቂቶች የሚዘወረው የንዋይ ግዝፈት ድንገት ከፍተኛ ችግር ውስጥ የወደቀው፥ ለሚታለቡት ላሞች ቀለብ በመንፈጉ ነው፡፡ ህገ-ማህበረሰብ በህገ-ግላዊነት ተተክቶ በመቆየቱ፥ ያመቸውና የቻለ ሁሉ ያለምንም ገደብና ቁጥጥር ሲጋልብ፥ ንዑሳኑ በሃብታቸውና በዝናቸው “ሰማይ” ቢደርሱም፥ ብዙሃኑ መሠረታዊ ፍላጎቶቹን ማለትም የዕለት ጉርሱን፥ ልብሱንና መጠለያውን በአግባቡ ማግኘትና መከላከል ያልቻለበት ሁኔታ ተፈጠረ፡፡ የብዙሃኑ መራቆት ለጥቂቶቹ ስግብግብ ባህርይ ምርኩዝ ሆኖ ማገልገሉን መቀጠል ባለመቻሉም፥ የካበተው ንዋይ መንቀሳቀስ አቃተው፤ በዚህም ምክንያት የዘመናችን 'በልተህ ተቀደስ' ሥርዓት በቀላሉ የማይወጣው ችግር ገጠመው፡፡ ለሰው ዐይን የረቀቀ የሃብት ቁልል ከመቅጽበት ከቁጥር ጣሪያ ተምዘግዝጎ እንጦሮንጦስ መውረዱ የሚነገረውና በእጥፍ ድርብ ተመንዝሮ እዳው የተረፈው ሕዝብም 'ምን ይከተል ይሆን?' በሚል የሰመመን ህልም ውስጥ ሰጥሟል፡፡

“በታላቋ” አሜሪካ ተቀስቅሶ ዓለምን ያናወጠው የንዋይ ቀውስ 'ሀ' ሲል የጀመረው እንደፈለጉት እንዲሆኑ የፈቀደላቸውን “ከእኔ በላይ ንፋስ” የምጣኔ ሐብት ሥርዓት መሠረት በማድረግ፥ ስግብግብነት በናጣቸው ጥቂት አልጠግብ ባዮች ምክንያት ነው፡፡ እነዚህ ንዋይ ያሰከራቸው ጥቅመኞች፥ ሃብታቸውን የጎዘጎዙት በቀላሉ ለመጥመድ አመች ሆኖ ባገኙት የብዙሃኑ መሠረታዊ ፍላጎቶች ላይ ነው፡፡ ግለሰቦች መጠለያ ቤቶቻቸውን ያለችግር ከገቢያቸው ጋር ተመጣጣኝ ባልሆነ ሁኔታ ተበድረው መግዛትና መሥራት ይችሉ ዘንድ የፋይናንስ ተቋሞች ማበደሪያ ጽ/ቤቶቻቸውን በመክፈትና ንጹሃን ዜጎች ቁሳቁስ ልብሳቸውንና የፍጆታ ወረታቸውን ባሰኛቸው ጊዜና ቦታ ላይ አግኝተው እንዲጠቀሙ ፕላስቲክ ገንዘብ በማመቻቸትና በመሳሰሉት መሳሪያዎች ህብረተሰቡ ተተበተበ፡፡ በ“በልቸው ልሙት” የተገባው ይህ እዳ ግን፥ በየሰኮንዱ እላፊ በአናት ላይ እየተቆለለ በመምጣቱ የሚያርጠውን የወለድ እዳ ተበዳሪው ቀስ በቀስ ሊከፍል ከማይችልበት ደረጃ ደረሰ፡፡ ዜጎች ቤታቸውንና ንብረታቸውን አናድናለን በሚል ብዙ ጥረው፥ የሥራ አቅማቸውንና ቀሪ ንብረታቸውን ሁሉ ገብረው አልሳካ ሲላቸው ያቆሙትን ቤትና ያለየሌለ ሃብታቸውን ከስረው እየሸጡ፥ ወይም ለአበዳሪው እያስረከቡ ዕድላቸው በሰፈረችላቸው ተወሰኑ፡፡ በዚህ አይነት ሁኔታ ብዛት ያላቸው ባለእዳዎች እየከሰሩና ለአበዳሪ የንዋይ ተቋሞች እያስረከቡ ሲገለሉ፥ በአንድ ወቅት ለሃብታሞች የማያቋርጥ የገቢ ምንጭ የነበሩ የሰው ልጆች ጠፉ፡፡ በትርፍ ላይ ትርፍ እያካበተ ይሽከረከር የነበረው ካፒታልም መራገፊያ አጥቶ ተሰቅዞ ተያዘ፡፡ ብዙሃኑ ሲደኸዩና የመግዛት ፍላጎት ሲያሽቆለቁል፥ የሸቀጥ እቃዎች ሸማችና ገዥ ያጣሉ፤ ሸቀጦችን የሚገዛቸው ሲጠፋ፥ እነዚህን ሸቀጦች ያመርቱ የነበሩ እልፍ አእላፍ ሠራተኞች ከሥራ ይባረራሉ፡፡ እንዲህም እያለ ይህ ችግር እንደሰንሰለት በተያያዘውና እጅግ ስፋት ባለው የአሜሪካ ካፒታል ተቋሞችና የኢኮኖሚ አውታሮች ላይ ላይ የሚያንዘፈዝፍ ንዝረት ዘራባቸው፡፡

ላለፉት 20 ዓመታት ያህል፥ ብቸኛዋ ሃያል መንግሥት አሜሪካ በዓለም አቀፍ ደረጃ ከፍተኛ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ተጽእኖ አድርጋ መቆየቷ ይታወሳል፡፡ የተመቻቸላትና በብቸኝነት ያያዘቺው ዓለምም ቢያንስ በኢኮኖሚያዊ ሥርዓቱ የሷን ፈለግ እንዲከተል ከማበረታታቷና ከመታገሏም በላይ፥ ብዛት ያላቸው አገሮች በፍላጎታቸው የአሜሪካዊው “ስድ” የገበያ ኢኮኖሚያዊ ሥርዓት ባለቤት ለመሆን የየበኩላቸውን ጥረት አድርገዋል፡፡ በዚህም የተነሳ ከዘመኑ የመገናኛ እድገት ጋር ተያይዞ አብዛኛው የዓለማችን ኢኮኖሚ በአሜሪካ ጥላ ሥር የወደቀና እርስ በርሱ ተያይዞ የተወራረሰ ሆነ፡፡ በመሆኑም፥ የሥርዓቱ ቁንጮ የሆነው የአሜሪካ ኢኮኖሚ ዕድገቱን ጨርሶ ወደ ቁልቁል ሲዘም፥ በየሀገሮች ውስጥ ከፍተኛ ኢኮኖሚያዊ መናጋት ተፈጠረ፡፡ የታንክና የመትረየስ ድምጽ የማያጓራበት፥ ነገር ግን መውጫና መግቢያ ያሳጣ ከፍተኛ የሆነ ጦርነት በየሀገሮች ውስጥ ተከፈተ፡፡ ምን ያህል ጊዜ እንደሚዘልቅና እንዴትስ ተካሂዶ የት ላይ እንደሚፈጸም ሚያውቅ አልተገኘም፡፡ የየሀገሮች መንግሥታት ይሆናል ያሉትን አማራጭ ሁሉ እየወሰዱ ሲሆን፥ ለጊዜው በፍቱህነት እየታየ ያለው መፍትሄ የመንግሥት ተሳትፎ ሚና ጉልህ የመሆኑ አስፈላጊነት ነው፡፡ አሜሪካን ጨምሮ ብዙ የምዕራቡ አገሮች ሊወድቁ ለሚንገዳገዱ የግል ተቋሞች መደገፊያ ገንዘብ ከመለገሳቸውም በላይ፥ በቀጥታ እሴቶቻቸውን በንብረትነት እየያዙ ነው፡፡ ይህም አካሄድ በምሁራኑና በፍልስፍናው አካባቢ ትልቅ ትኩረት ፈጥሮ ሥርዓተ ማህበራት ከውስጣቸው በቅሎ ባደገ ቅራኔ ሲወጠሩ ከየት ወደየት ሊሸጋገሩ እንደሚችሉ መልስ ለመስጠት ውይይቱ ተሚሙቆና ጡፎ ይገኛል፡፡ አንዳንድ በግራው አመለካከት የከረሙ ምሁራንና ፈላስፎች የባህረ ሃሳባቸው ርዕቱነት መረጋገጡ ሲሰማቸው፥ ማህበረሰባዊ የኢኮኖሚ ሥርዓትን እንደ ዳቢሎስ ይመለከቱ የነበሩቱም፥ ኢኮኖሚያዊ ሥርዓት እንግዲህ ቢያንስ፥ አሜሪካ ታራምደው በነበረው ቁጥጥር አልባ ሁኔታ ሊገነባና ሊራመድ እንደማይችል ግንዛቤ ያደረጉ ይመስላል፡፡ ይሁን እንጅ አሁን ዓለማችን የገባችበት የኢኮኖሚ ቀውስ እንዴት እንደሚጠገንና ሊደላደል እንደሚችል ግን አፉን ሞልቶ የሚናገር አልተገኘም፡፡ ይህም ሁኔታ በየሀገሮች ውስብስብ የሆነ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ቀውስ በአጭር ጊዜ ውስጥ ሊፈጥር ይችላል፡፡

ከሥራ የተባረሩ በብዙ ሺዎች የሚቆጠሩ ሠራተኞች የኢኮኖሚ ጥያቀዎች ሊያነሱ ይችላሉ፡፡ ዝርፊያና ቅሚያ ተስፋፍቶ በአንዳንድ ሀገሮች ህገወጥነት ሊነግሥ ይችላል፡፡ በትላልቅ መንግስታት ሥር ሁለመንተናቸውን ሸጉጠው የቆዩ ታናናሽ መንግሥታት ለሠራዊታቸው፥ ለደህንነት ጠባቂዎቻቸው፥ ለመንግሥት ሠራተኞቻቸውና ለመሠረታዊ ጉዳዮች ሁሉ የሚያውሉት ተንቀሳቃሽ ገንዘብ ሊነጥፍባቸው ይችላል፡፡ አልባሌ መንግሥታት የውስጥ ችግሮቻቸውን አቅጣጫ ለመቀየር ሲሉ ዳር ድንበራቸውን እያለፉ ነገር በመጫር አላስፈላጊ የሆኑ ጦርነቶችን ይከፍቱ ይሆናል፡፡ አምባገነን ገዥዎች ምንም እንኳ አድራጎታቸው የበለጠውን ችግር ውስጥ ሊያስገባቸውና ፍጻሚያቸውን ሊያፋጥነው ቢችልም፥ አፍነው ይዘው ለመግዛት በማሰብ በዜጎቻቸው ላይ እጅግ ጨካኞችና አረመኔዎች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

ግራም ነፈሰ ቀኝ፥ ይህ ሁሉ ያልፍና ብሩህ ጊዜ ይመጣል፡፡ ጊዜያችንና ሃይላችን ሁልጊዜ ለጋራ ልእልና ገንቢ በሆነ ተግባር ላይ እናውለው፡፡ ለራሳችን መልካሙን ስንመኝ ለመሰሎቻችንና ከእኛ በታች ላሉ ሁሉ እንስብላቸው፡፡ ያንዱ ወደ ሁዋላ መቅረት ቀድሞ መራመድ የሚሻውን ይጎትታል፤ ጥቂቶች ሩጠው ሲያሸንፉ ብዙሃኑ በፍቅር ተመስጦ ካላንጨበጨቡላቸው ተመልካቹ ሕዝብ ጥያቄ አለው፡፡ የሰውን ልጆች ደህንነትና ሰላማዊ ኑሮ ግምት ውስጥ ያላስገባ ብልጽግና ማህበራዊ ይዞታ የለውም፡፡ የተግባር ውጤቶቻችን ሁሉ ማህበራዊ ይዘት ከሌላቸው ደግሞ ፈጣሪዎቻቸውን መልሰው የሚበሉ ሰው-ሠራሽ ክስተቶች ይሆናሉ፡፡ በግለሰብ ደረጃም እያንዳንዳችን ሃላፊነት እንዳለብን መዘንጋት የለብንም፡፡ የማንችለውን አንሸከም፤ ዘለቄታ ለሌለው ጊዜያዊ ጥቅም ተላላዎችና ተጎታቾች አንሁን፡፡ ψ